# እንኳን ደስ ያለሽ !



(ቀደም ሲል የዓለም - አቀፍ ሴቶች ሚዲያ ፋውንዴሽን፣ በቅርቡ ደግሞ የዩኔስኮን የነጻ ፕሬስ ሽልማት ላገኘችው ጋዜጠኛና መምህርት ርዕዮት አለሙ መታሰቢያ)




ለነጻነቴ ስትሟገቺ ለመከራ የተዳረግሽ እህቴ ሆይ !
"ብረሳሽ ቀኜ ትርሳኝ" ክቡር ቃል ለምድር ለሰማይ።

ንጹህ ሃሳብሽን ስለገለጽሽ፣
ያለጥፋት ያለበደልሽ፣
በፍርደ - ገምድል በግፍ ታሰረሽ፤
ሕመም ስቃይሽን ችለሽ፣
መቀነትሽን ጠበቅ አርገሽ፣
ለአንዲት ሐቅ በክብር የቆምሽ፣
ርዕዮት ሆይ ! ወህኒ ያለሽ፤

አሳሪሽ ነው ያፈረ፣
በሞራሉ የከሰረ፣
በተግባሩ የተነወረ፣
እኩይ ሥራው ሲሞግተው . .
እንቅልፍ አጥቶ ያደረ፤

እንደሱ ከመኖር ብለሽ . .
በሐኬት ቆፈን ተይዞ፣
አንቺማ ተወጣሽው . .
የሐሴትን መንገድ ጉዞ፤
ዓለም አወቀው ፈለግሽን . .
በተፈጥሮ መብት የታነጸ፣
ለሕዝቦች ክብር ያለመ . .
ባምባገነኖች ላይ ያመጸ፤

ይደልዎ ! ይደልዎ ! ይገባሻል ሽልማቱ፣
እመ - እምነቴ፣ ነጻነቴ - ለሃቅ የቆምሽ አንቺ ብርቱ !




Columnist Reeyot Alemu




---

ጌታቸው አበራ
ሚያዝያ 2005 ዓ/ም
(አፕሪል 2013)